አይ ቲ ፒ

# የምርምሬ ትኩረት 2001 ኢ.ም.

## -አማርኛ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል, አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ኅዳር-መጋቢት 2001 ኢ.ም.)-


የአሣፋስ ኪዮቶ ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ አመት ተማሪ

ዩኢ ሱናኖ


እኔ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ዉስጥ የኢትዮጵያን የግብርና ሁኔታ በማጥናት ላይ እገኛለሁ። የኔ ዋና የጥናት ቦታ ደግሞ የደራሼ ልዩ ወረዳ ሲባል ይኈ ወረዳ የተለያዩ የአየር ንብረቶች የያዘ ወረዳ ነው። በኢትዮጵያ በተለይም ከቅርብ ጊዜያት ወድህ ለውጭ ገበያ ሲባል በተለይም አለምአቀፋዊ እውቅና ያላቸውን ምርቶች ሌላውን እየተኩ የመምጣት ሁኔታ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ነው። ለምሣሌ በብዛት የጤፍ ምርት ሁኔታ የመጨመር ሁኔታ ይታያል(ማከይን 2001፤2007)።

ስለዚህ የኔ ዋነኛው የጥናት ትኩረት በተለይ አሁን በብዛት በኢትዮጵያ እየተሰፋፋ የመጣውን ለገበያ የሚመረቱ የእርሻ ሠብሎች መጠን መጨመር አገር በቀል በሆኑት የሠብል ምርቶች ላይ የሚያሣድሩትን ጫና ማጥናት ነው። ለምሣሌ አገር በቀል ያልሆነው የበቆሎ ምርት በብዛት መስፋፋት አገር በቀል በሆነው የጤፍ ምርት ላይ የሚያሳርፈውን ጫና ማጥናትና መረዳት ነው።

በተጨማርም ይህ ሁኔታ በተለይም የአርሶ አደሩን የአኗኗር ዘይቤ በመለወጥ ረገድ የሚያሳድረውን ጫና ለመዳሠ እቅድ አለኝ ። ይህ የጥናት አካሄድ ሁለት ነገሮች ላይ ትኩረት ያዳርጋል። የአመራረት ዘዴ የአኗኗር ዘይበ ነጸብራቅ መሆኑንና ሁለቱም የታያያዙና አንዱ የለላው ውጤት መሆናቸውን ለማሣየት የሚሞከር ጥናት ነው።

በቅርቡም የዚህ አይነት ሁኔታ የኔ ልዩ የጥናት ቦታ በሆነው በደራሼ ልዩ ወረዳ የሚገኘው የአልጉሃ መንደር ውስጥ እየታየ ነው። በዚህ የኔ የጥናት ስፍራ በሆነው ቦታ አሁን በስፋት እየተመረተ የሚገኘው ሠብል በቆሎ ነው።

ከዚህ ቀደም ግን በአልጉሃ በዋነኛነት ይመረት የነበረው ሰብል ማሽላ ነበር። የማሽላ መንደርነቷን ለማንጸባረቅም አልጉሃ በቅጻል ስሟ የማሽላ አልጋ በመባል ትታውቅ ናበር። አሁን ግን የመንደርዋ ነዋሪዎች በቆሎን በዋነኛ ምግብነትና እንድሁም ለገበያ በማውጣት የሚሸጡት ምርት, አድርገውታል። በአሁኑ ወቅት በማህበረሰቡ ዘንድ ማሽላ የሚያገለግለው የባህል መጠጥ ለሆነው ቻጋ ለመጥመቅ ብቻ ሆኗል። በአሁን ሰአት በተለይም የኔ የጥናት ማዕከል በሆነው በአልጉሃ የማሽላ ማምረቱ ሂደት በበቆሎ የተተካ ሲሆን ይህንን የእርሻ ሠብል ምርት ለውጥ እንድሁም እሱን ተከትሎ በነዋሪዎችዋ ዘንድ የመጣውን የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ በአልጉሃ መንደር ላይ ትኩረት አድርገ ሣይንሣዊ ጥናት በማድረግ ላይ እገኛላሁ።